ፒስ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ
PEACE MICROFINANCE S.C

PEACE/651/22

ኖቬምበር 26, 2022
ሕዳር 17 ቀን 2015 ዓ.ም

ለ ____________________
<u>አዲስ አበባ፤</u>

ጉዳዩ:- <u>የባለአክሲዮኖች 26ኛ መደበኛ ጉባኤ የስብሰባ ጥሪ</u>

ፒስ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ የተከፈለ ካፒታል ብር 30,324,000 (ሰላሳ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃያ አራት ሺህ ብር)፣ የምዝገባ ቁጥር MFI/012/2014፣ ዋና መ/ቤት በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 198 ልዩ ቦታው መስቀል ፍላወር ሆቴል ጀርባ የሚገኘው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጉባዔ በቀን **ታህሣሥ** 15, 2015 (ዲሴምበር 24, 2022) የሚያካሂድ በመሆኑ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት ጀምሮ ባለአክሲዮኖች መደበኛ ጉባዔ ላይ እንድትገኙልን የዳይሬክተሮች ቦርድ በአክብሮት ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

## የመደበኛ ጉባኤ አጀንዳዎች

1) ድምፅ ቆጣሪዎች መሰየምና ማፅደቅ፤
2) ምልዓተ ጉባኤ መሟላቱን ማረጋገጥ፤
3) የጉባኤውን ረቂቅ አጀንዳ ማፅደቅ፤
4) እ.ኤ.አ. የ2021/2022 የዳሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማጽደቅ፤
5) እ.ኤ.አ. የ2021/2022 የውጭ ኦዲተሮች ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማጽደቅ፤
6) የአክሲዮን ማህበሩን የሂሳብ ሚዛን ማጽደቅ፤
7) እ.ኤ.አ. በ2021/22 በተገኘ ትርፍ የአባላትን የአክሲዮን ድርሻ ስለማሳደግ ተወያይቶ መወሰን፤
8) የማሕበሩ የተጠራቀመ ትርፍ (Reatained earning) የአባላትን የአክሲዮን ድርሻ ስለማሳደግ ተወያይቶ መወሰን፤
9) የተከናወኑ የአክስዮን ዝውውሮች ማጽደቅ፤
10) በለቀቁ ዳይሬክተሮች ምትክ በዳይሬክተሮች ቦርድ የተተኩ ዳይሬክተሮችን ሹመት ማጽደቅ፤
11) የጉባኤውን ቃለ-ጉባኤ ማጽደቅ ናቸው፡፡

ከሠላምታ ጋር

*<u>አድራሻ</u>፤ ቂርቆስ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 198 መስቀል ፍላወር ጀርባ በሚገኘው በዋናው መ/ቤት (ANAD ሕንጻ አጠገብ)*

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ስልክ +251-011 652 15 41 ፋክስ +251-011 557 19 26 ፖ.ሣ.ቁ: 5743